# "መስመር እየ ኃይሉና!" እስከመቼ?

## ህወሓት እና የወደፊት ዕጣ-ፈንታው

ልደቱ አያሌው

ጥር 17 2016 ዓ.ም

# “መስመር እዩ ኃይልና!” - እስከመቼ?

## ህወሓት እና የወደፊት ዕጣ-ፈንታው

ትግራይ በኢትዮጵያ የአገር ምስረታ ሂደት የነበራት ሚና ዓይነተኛ (Core) ሊባል የሚችል ነው። ትግራይ የብዙ ቀደምትና በጎ ስልጣኔዎች መነሻ፣ በአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ዋና የስልጣን ተቀናቃኝ፣ የውጭ ኃይሎች መግቢያና መውጫ የነበረች ስትራቴጂክ ግዛት በመሆኗ ባለፈው ብቻ ሳይሆን በዛሬውም ሆነ በወደፊቱ የአገራችን የፖለቲካ ሂደት የጎላ ሚና ይኖራታል።

ከትግራይ የተፈጠረው ህወሓት ለአለፈው ግማሽ ክፍል-ዘመን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት የነበረው ሚና ከፍተኛ ነው። ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችን አስተባብሮ ደርግን በመጣልም ሆነ በኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን የመሪነት ድርሻ ይዞ በአገሪቱ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ለውጥ በማምጣት ረገድ ህወሓት የነበረው ሚና ሚዛን የሚደፋ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላም “የኮንፌደሬሽን” ሃይሎችን በመቀሌ በማሰባበሰብና የአዲሱ አገዛዝ ቀንደኛ ተቃዋሚ በመሆን፣ ጦርነት ከተጀመረ በኋላም የትግራይ ህዝብ ለህልውናው መቀጠል በአካሄደው የትጥቅ ትግል የመሪነት ድርሻ በመያዝ የጎላ ሚና ተጫውቷል።

ይህ ለግማሽ ክፍለ-ዘመን የትግራይን፣ ለ27 ዓመታት ደግሞ የኢትዮጵያን ህዝብ ሕይወት ተቆጣጥሮ የኖረ፣ በዓላማ ፅናቱና በድርጅታዊ አቅሙ እጅግ አስደማሚ ብቃት የነበረው ጠንካራ ድርጅት ከፕሪቶሪያው የሡላም ስምምነት በኋላ ግን በአገሪቱ ፖለቲካ የነበረውን የጎላ ሚና ከማጣቱም በላይ ትግራይን በአግባቡ መምራትም ሆነ የራሱን ድርጅታዊ ህልውና አስጠብቆ ለማስቀጠል እየተሳነው ነው። ለትግራይ ህዝብ ህልውና ስታገል ኖርኩ የሚለውና እስካሁንም ድረስ “የትግራይ ነፃ አውጭነት” ስሙን ያልቀየረው ህወሓት ዛሬ ላይ የትግራይን ህዝብ በመድሃኒት እጦትና በረሃብ ከመሞት ለማዳን የተሳነውና በስልጣን ሽኩቻ ጊዜውን ሲያባክን የሚውል ደካማ ድርጅት ሆኗል። በዚህም ምክንያት “ህወሓት ይፍረስ ወይስ ይቀጥል?” የሚለው ጥያቄ በመሃል አገር ብቻ ሳይወሰን በትግራይ ህዝብና ልሂቃንም ዘንድ የወቅቱ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል።

ህወሓት ለሰራቸው ስህተቶችና ጥፋቶች የከረረ ትችትና ውግዘት የሚቀርብበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአንፃሩ ለሰራቸው በጎ ነገሮች ግን ተገቢ እውቅናና ምስጋና የተነፈገው “አመድ-አፋሽ” ድርጅት ነው ማለት ይቻላል። በ27 ዓመቱ ህወሓት መራሽ የኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን በታሪካችን አይተነው በማናውቀው መጠንና ፍጥነት ከፍተኛ የማህበረ-ኢኮኖሚ ለውጥ በአገሪቱ ታይቷል። መንገድ፣ ግድብና አየር ማረፊያን በመሰሉ መሰረተ ልማቶች፤ በትምህርት፣ በጤና፣ በመገናኛ፣ በመብራትና ውሃ አገልግሎት መስፋፋት፤ በቤቶች ልማት፤ በኢንዱስትሪ መስፋፋት፤ በድህነት ቅነሳ፤ ወባንና ኤች-አይ-ቪ ኤድስን የመሳሰሉ ገዳይ ወረርሽኞችን በመቆጣጠር፤ በነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገትና በአጠቃላይ የሚሊኒየሙን የልማት ግብ በማሳካት ረገድ የመጣው ለውጥ (ከእነ ህፀፆቹ) እጅግ ከፍተኛ ሊባል የሚችል ነው።

የመጣው ለውጥ ከለውጥም ባለፈ በአንፃራዊ የመዋቅር ሽግግር ደረጃ ሊገለጽ የሚችል ነው። 2010 ዓ.ም ላይ ዘመናዊ የእጅ ስልክ ይዘው ማህበራዊ ሚዲያን መጠቀም የጀመሩ፣ ኮሌጅ ገብተው መማርና መብታቸውን አውቀው መጠየቅ የቻሉ የትውልድ አባላት አምጸው የአገዛዙን ህልውና ሲፈታተኑ ያየነውም

ያለምክንያት ሳይሆን ኢህአዴግ ራሱ በኢኮኖሚና በአስተሳሰብ አብቅቶ ባሳደገው ትውልድ ጭምር የጥቃት ተጋላጭ በመሆኑ ነው።

ይሁንና ከፖለቲካና ከሰብዓዊ መብት ጥበቃ፣ ከህገ-መንግሥታዊነት፣ በተለይም ከህዝብ አንድነትና ከአገር ህልውና አኳያ ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ የሰራው ጥፋት በዚያው መጠን እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ አገሪቱ ዛሬ ላይ ለምትገኝበት አጠቃላይ ቀውስ መፈጠር ዋና ምክንያት የሆነ ነው። ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች ለመጀመሪያ ጊዜ እውቅና እንዲያገኙና አንጻራዊ ሠላምና የህግ የበላይነት በአገሪቱ እንዲኖር በማድረግ ረገድ ኢህአዴግ አንፃራዊ ጥንካሬ እንደነበረው መካድ አይቻልም። ነገር ግን መብቶች ከህግ ድንጋጌነት አልፈው በተግባር እንዳይኖሩ፣ የጽንፈኝነትና የብሔርተኝነት ፖለቲካ የበለጠ መዋቅራዊ ሆኖ እንዲስፋፋ፣ ያልተገቡና ልዩነትን መሰረት ያደረጉ ትርክቶች በስፋት እንዲሰበኩ፣ የሙስናና የወገንተኝነት ባህል እንዲጠናከር፣ አገሪቱ የባህር-በር እንድታጣ፣ በአጠቃላይ የህዝብና የአገር አንድነት እንዲዳከምና በመጨረሻም የህልውና አደጋ ላይ እንዲወድቅ በማድረግ ረገድ ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።

በ1983 ዓ.ም ላይ ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ ለስልጣን ሲበቃ የአገሪቱ ህዝብ ቁጥር ከ50 ሚሊዮን ያልበለጠ ነበር። ማለትም ከ70 ሚሊዮን (ከ55%) በላይ የሆነው ህዝብ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ የተወለደ ነው። እንዲያውም ከፖለቲካ አመለካከት ስርፀት አኳያ በአነስተኛ ግምት ከ100 ሚሊዮን ያላነሰው የትውልዱ አባል የኢህአዴግን ብሔር-ተኮር ፖለቲካ ሲሰማ ያደገና በአገዛዙ አስተሳሰብ የተቀረጸ ነው። እውነታው ይህ ሆኖ እያለ ኢህአዴግ ለምን ራሱ በፈጠረውና ተቆጣጥሮት በኖረው ትውልድ አማካኝነት የመጠቃት ፈተና ገጠመው? ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከልስ የበለጠ ጥንካሬ የነበረው ህወሓት ለምን ከሌሎች ተለይቶ የመጠቃትና የህልውና ፈተና ላይ የመውደቅ አደጋ ገጠመው? በህወሓት ላይ የሚደርሰው ጥቃትስ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን እራሱ ከፈጠራቸው ወይም አጠናክሮ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ካደረሳቸው የኢህአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ጭምር ለምን ሊመጣ ቻለ? እነዚህንና እነዚህን መሰል ጥያቄዎች ነፍስን የመመርመር ያህል ደፋርና ሃቀኛ ግምገማ ማድረግን ይጠይቃል። ግምገማ ማድረግን ተከትሎም የአመለካከትና የአሰራር ድክመቶችን ከልብ ማረም፣ ለአለፉ ጥፋቶችና ስህተቶች ልባዊ ጸጸትና ቁጭት ማሳየት፣ ከተቻለና ድፍረቱ ከተገኘም ህዝብን ልባዊ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ እውነተኛና ዘላቂ መፍትሄ ለመሻገር አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎች ናቸው።

በእኔ እይታ በ2010 ዓ. ም በአገራችን መጣ የተባለው "ለውጥ" እንዳይከሽፍ ከተፈለገ ለጊዜው ኢህአዴግን ማፍረስ አይጠቅምም ብዬ እንደተከራከርኩት ሁሉ፣ ዛሬም የትግራይ ህዝብ ከገጠመው ሁለንተናዊ አደጋ ለመውጣት ይችል ዘንድ መፍትሄው ህወሓትን አሁን ላይ ማፍረስ ሳይሆን አንዱ የመፍትሄው አካል ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ነው እላለሁ። ህወሓት "መስመር እዩ ኃይልና" ከሚለው የፖለቲካ ርዕዮትን እንደ ሃይማኖታዊ ቀኖና የመቁጠር ግብዝ አመለካከቱ በድፍረት ሰብሮ መውጣት ከቻለ፣ ራሱን እንደ ብቸኛ ሳይሆን እንደ አንድ አማራጭ ፓርቲ ከቆጠረ፣ መሰረታዊ ድክመቶቹን በሃቅና በድፍረት ገምግሞ ራሱን ማረምና ማጠናከር ከቻለ በትግራይም ሆነ በአገሪቱ የወደፊት የፖለቲካ ሂደት ገንቢ ሚና ለመጫወት

ይችላል፤ ይገባልም ብዬ አምናለሁ። ህወሓት በአሁኑ ወቅት መፍረስ የለበትም የምለውም በዋናነት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

**አንደኛ፡-** ከተግባራዊነት አኳያ ቀላል በማይባል የትግራይ ህዝብና በህወሓት መከከል ያለው የረዥም ጊዜ ስሜታዊነትን የተላበሰ (Sentimental) ግንኙነት በሂደት እንጂ በቀላሉ ሊለያይ አይችልም።

**ሁለተኛ፡-** ህወሓት ድክመት ብቻ ሳይሆን ጥንካሬም ያለው አንጋፋ ድርጅት በመሆኑ ለመጪው የትግራይ ትውልድ እርሾ ሆኖ የሚጠቅም እሴት አለው።

**ሦስተኛ፡-** የሰሜን (የአቢሲኒያ) ኃይሎችን በማዳከም የስልጣን ዕድሜዬን ማራዘም እችላለሁ ብሎ የሚያስብ አገዛዝ ባለበት በአሁኑ ወቅት ህወሓትን ማፍረስ የትግራይን ህዝብ ለበለጠ ጥቃት ሊያጋልጥና የአገሪቱን የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍም የበለጠ ሊያዛባ ይችላል የሚል እይታ ስላለኝ ነው።

## ህወሓትና የትግራይ የፖለቲካ ማህበረሰብ መግባባት ሊፈጥሩባቸው የሚገቡ አወዛጋቢ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?

በእኔ እይታ በህወሓትና በትግራይ የፖለቲካ ማህበረሰብ ዘንድ በትኩረት ውይይትና ግምገማ ሊካሄድባቸው ይገባል ብዬ የማምንባቸው ጥያቄዎች ከሞላ-ጎደል የሚከተሉት ናቸው።

1. አገሪቱ በአሁኑ ወቅት የገባችበት የፖለቲካ ቀውስ በምን ደረጃ ይገለፃል? ለምንስ ወደዚህ ዓይነቱ ቀውስ ውስጥ ገባች? ለዚህ ቀውስ መፈጠር የትግራይና የህወሓት ልሂቃን ድርሻ ምን ነበር?
2. ህወሓት እስካሁን ያራመደው ግራ-ዘመምና ብሔር-ተኮር የፖለቲካ መስመር ምን ውጤት አምጥቷል? ምንስ ጉድለት ነበረበት?
3. ህወሓት የኢትዮጵያንና የትግራይን ያለፈ ታሪክ በተመለከተ ያራምድ የነበረው አቋምና ትርክት ምን ጉድለት አለበት?
4. ህወሓት የኢትዮጵያን አንድነት፣ የኤርትራን ጥያቄና የባህር-በር ጥያቄን በተመለከተ ያራመደው አቋም ምን ያህል ትክክል ነበር?
5. ህወሓት "የአማራ ገዢ መደብ"፣ "ነፍጠኛ"፣ "ትምክህተኛ" በሚሉ ፍረጃዎች ያራመዳቸው ትርክቶች በትግራይና በአማራ ህዝብ ግንኙነት የፈጠሩት አንደምታ ምንድን ነው? ወልቃይትና ራያ የሁለቱ ህዝቦች የቅራኔ ቦታዎች ለምን ሆኑ? ይህ እንዲሆን የህወሓት ሚናና ድርሻ ምን ነበር?
6. ከ29 ዓመት በኋላ ህወሓት የአገሪቱን ህገ-መንግሥት በተመለከተ ምን የአመለካከት ለውጥ አለው? በተለይም የመገንጠል መብት እውቅና ማግኘቱና ቋንቋን መሰረት ያደረገ የፌደራል አከላለል በተግባር መዋሉ የትግራይንም ሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ በአጠቃላይ ምን ጠቀመ?

7. ዶ/ር ዐቢይን የመሰለ ደካማና አደገኛ ሰው በኢህአዴግ ምክር ቤት ተመርጦ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዲበቃ በማስቻል ረገድ የህወሓት ሚና ምን ነበር?
8. ለሁለት ዓመቱ የትግራይ ጦርነት መነሳትና በህዝቡ ላይ ለደረሰው እልቂት የህወሓት ድርሻ ምን ነበር? ከዚህ ጦርነትስ ምን ትምህርት ተቀስሟል?
9. የኤርትራ መንግሥት ጊዜ ጠብቆ በትግራይ ህዝብ ላይ በቀል እንዲፈጽም ዕድል በመፍጠር ረገድ የህወሓት ሚና ምን ነበር? ኤርትራን በሚመለከት የህወሓት የወደፊቱ አቋም ምን ሊሆን ይገባል?
10. ህወሓት ከ50 ዓመት የትግል ተሞክሮና ሂደት በኋላ ለምን የስትራቴጂክ አመራር እጦት ገጠመው? የአመራር ችግሩን ለመፍታት ምን መደረግ አለበት?
11. በትግራይ ሰብዓዊ መብት እንዳይከበር፣ የብዙሃን ፓርቲና የዲሞክራሲ ስርዓት በበቂ መጠን እንዳይኖር፣ ተፅዕኖ የበዛበት የነፃ ገበያ እንዲኖር፣ ህዝቡ ከድህነት ኑሮ እንዳይላቀቅ በማድረግ ረገድ የህወሓት ሚና ምን ነበር?
12. በህወሓትና በብልጽግና ፓርቲ መካከል ያለው የወቅቱ ግንኙነት ጤናማና ተገቢነት ያለው ነው? ወደፊትስ በምን አግባብ ሊቀጥል ይባል?
13. በአማራና በትግራይ ህዝብ መካከል ያሉት ቅራኔዎች ዘላቂ ሠላምን በሚያሰፍን አግባብ እንዴት ሊፈቱ ይገባል?
14. የትግራይ ህዝብ አሁን ላይ የገጠሙት መሰረታዊ ችግሮች በቅደም ተከተል ምን ምን ናቸው? እንዴትስ በዘላቂነት ሊፈቱ ይችላል?
15. ኢትዮጵያ አሁን ላይ ከምትገኝበት አጠቃላይ ቀውስ እንዴት ልትወጣ ትችላለች? ለመፍትሄው የህወሓት ድርሻና ሚና ምን ሊሆን ይገባል?
16. ህወሓት ደርግን በማስወገድ ረገድ ቁልፍ ሚና መጫወቱና በ27 ዓመቱ የኢህአዴግ ስርዓት የመሪነት ድርሻ ይዞ የሰራቸው በጎ ነገሮች ለምን ተገቢ ትውስታና ምስጋና ሳይቸራቸው ቀረ? በመጡት ለውጦች ተጠቃሚ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችና የኢህአዴግ አባልና አጋር የነበሩ ድርጅቶች ጭምር እንዴትና ለምን የዚህ "ውለታ ቢስነት" ባህሪ ሰለባ ሆኑ? የሚሉ ናቸው።

ከእነዚህ 16 ጥያቄዎች በተጨማሪ ከወንጀል ተጠያቂነትና አገራዊ መግባባት ጋር የሚያያዙ ተጨማሪ ጉዳዮች እንዳሉ እገነዘባለሁ። ነገር ግን እንደዚህ አይነቶቹ ጉዳዮች ሁሉን-አቀፍ በሆነ አዲስ የሽግግር ሂደት በሚካሄድ የሽግግር ጊዜ ፍትህና የአገራዊ እርቀ-ሠላም ሂደቶች ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው ብዬ ስለማምን እዚህ ላይ እንዳይካተቱ ማድረጌ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል። የመሬት ባለቤትነትን የመሳሰሉ ቁልፍ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ያልተካተቱትም በህገ-መንግሥቱ ማዕቀፍ ይታያሉ ተብሎ በመታሰቡ ነው።

በእነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚካሔደው ግምገማና ውይይት በዋናነት መካሄድ የሚገባው ህወሓትን ማዕከል በማድረግ ቢሆንም - ትርጉም ባለው መጠን የትግራይ ልሂቃንን፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን፣ ሲቪክ ማህበራትን፣ ዳያስፖራውንና በዋናነት ህዝቡን በተለያየ ደረጃ የሚያሳትፍ መሆን አለበት። ከትግራይ ማዕቀፍ ባለፈ ህወሓትና የትግራይ ልሂቃን ከላይ ከተዘረዘሩት ጥያቄዎች አኳያ በሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የፖለቲካ ኃይሎችና ዓለም-አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ እንዴት ነው የሚታዩት? ለሚለው ተገቢ ጥያቄ ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ መወያየትና መልስ ማግኘት ይገባል። ከዚህ ውጪ ከሌላ ውጫዊ አካል የሚመጣን ትችትና ተቃውሞ

ሁሉ እንደ "ጠላት" አጀንዳ በመቁጠር፣ የፖለቲካ ርዕዮትንና መስመርን እንደ ሃይማኖታዊ ቀኖና በማምለክ፣ የአስተሳሰብ ለውጥን እንደ ሽንፈት በመቁጠር "ይህ" ወይም "ያ" ፖሊሲ የሚቀየረው "በመቃብራችን ላይ ነው" የሚል ፀረ-ዲሞክራሲያዊ መፈክር በማሰማት፣ የፖለቲካ ርዕዮትን ወይም የመስመርን ውድቀት ሁልጊዜም በአፈጻጸም ድክመት እያሳበቡ በመቀጠል የሚመጣ አዲስ ለውጥ አይኖርም። የእነዚህ ድክመቶች አጠቃላይ መገለጫ የሆነው "መስመር እዩ ኃይልና!" የሚለው የገነገነ የህወሓት መፈክር ከተፈጥሮም ሆነ ከማህበራዊ ሳይንስ የለውጥ ህግ ጋር አብዝቶ የተጣላ አመለካከት ነውና ሊለወጥ ይገባዋል። ህወሓት ብቻም ሳይሆን ህወሓትን እንደ "ጣዖት" የሚያመልኩ በቁጥር ቀላል የማይባሉ የትግራይ ተወላጆችም እንዲህ ዓይነቱን ስሜታዊና ኋላ-ቀር የሆነ አቋማቸውን በአግባቡ መመርመርና መቀየር ይጠበቅባቸዋል።

## ከ "መስመር እዩ ኃይልና!" ወደ "ዴሞክራሲ እዩ ኃይልና!"

ህወሓት በመቀሌ እያካሄደው ያለው ግምገማና ውይይት በስንትና በምን ዓይነት አጀንዳዎች ላይ እየተካሄደ እንደሆነ ባላውቅም ግምገማውና ውይይቱ 64 ቀናት እንደሆነው ሰምቻለሁ። ከሰሞኑ የአቶ ጌታቸው ረዳ ንግግር እንደሰማሁት ግን የትግራይ ህዝብ ረሃብና የስደተኞች ጉዳይ የስብሰባው አጀንዳ አልነበረም። ይህም በእጅጉ ይገርማል!

በአንድ አጀንዳ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ይበቃል? የሚለው ጥያቄ ሁሉን አግባቢ የሆነ መልስ ሊኖረው ባይችልም እኔ ባለኝ የረዥም ጊዜ የፖለቲካ አመራርነት ልምድ ለሁለት ወይም ሦስት ሠዓት በሚካሄድ አንድ ስብሰባ ላይ በአማካይ ከሦስት እስከ ስድስት አጀንዳዎችን መቋጨት የተለመደ ነው። ለምሳሌ ህወሓት ከሞላ ጎደል እኔ በዚህ ፅሁፍ በዘረዘርኳቸው 16 ጥያቄዎች ላይ ግምገማ ቢያካሂድና እጅግ በተጋነነ ግምት ለአንድ አጀንዳ አንድ ሙሉ ቀን ቢወስድበት በ16 ቀናት ውስጥ ግምገማውን ሊጨርስ ይችላል እንደማለት ነው። ከሞላ ጎደል በዚህ የእኔ ግምት ከተስማማን ታዲያ ለምንድን ነው ህወሓት ከ64 ቀናት በላይ የሆነና እጅግ የተንዛዛ ግምገማ የሚያካሂደው? የሚል ጥያቄ ልናነሳ እንችላለን።

በመጀመሪያ ደረጃ ከህወሓት ግንዛቤ በተቃራኒ የተንዛዛና ለረዥም ጊዜ የሚካሄድ ግምገማ የድክመት እንጂ የጥንካሬ መገለጫ አይደለም። የተንዛዛ ግምገማ በአጀንዳዎች ላይ አስቀድሞ ዝግጅት ካለማድረግ፣ በአጀንዳነት በቀረቡት ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤና እውቀት እንዲሁም የውይይት አመራር ችሎታ ከማጣት የሚመነጭ ድክመት ነው። በእኔ እይታ የህወሓት ድክመት ከዚህም በላይ ነው። ትልቁ የህወሓት የቆየ ድክመትና ችግር - በግምገማ ወይም በውይይት የሃሳብ መተማመንና መቻቻልን በመፍጠር የጋራ ውሳኔና ስምምነት ላይ ከመድረስ ይልቅ ሌሎችን በጫና በማሳመንና የራስን ሃሳብ በሌሎች ላይ በማስረጽ /Indoctrination/ የሚያምን ፀረ-ዴሞክራሲ ድርጅት በመሆኑ ነው።

ህወሓት ከምስረታው አስከ አሁን ድረስ ከትግራይ ህዝብ ስነ-ልቦናና ባህሪ በተለየ የዚህ ድክመት ሰለባ ሆኖ መኖሩን አምኖ መቀበል አለበት። ከማመንም ባለፈ “እንደገና መወለድ” በሚባል መጠን ራሱን ካልቀየረ በስተቀር ለአመታትም ቢሰበሰብ የተንዛዛ መግለጫ ከማውጣት ባለፈ አዲስና የተለየ መፍትሄ ይዞ ሊመጣ አይችልም። ህወሓት ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች በተሻለ ራስን የመገምገም ባህል ያለው መሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቢሆንም ፀረ-ዴሞክራሲ ከሆነውና ለውድቀቱም ዋና ምክንያቱ ከሆነው የግትርነት ባህሪው ትርጉም ባለው መጠን መላቀቅ ካልቻለ በስተቀር እንኳንስ ህዝብን ራሱን ከህልውና ጥፋት ሊታደግ አይችልም። በያዘው መንገድ ከቀጠለም ለመርዶ የማይበቃ አሟሟት ከሞተው ከብአዴን የተለየ ዕጣ-ፈንታ አይኖረውም።

በነገራችን ከላይ በዝርዝር ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች የራሴ መልስና አቋም አለኝ። ነገር ግን ህወሓት አንድ የመፍትሄ ሃሳብ ከሌሎች አካላት (በተለይም ከተቃዋሚው ጎራ ከመጣ በፍጹም ለመቀበል ያለመፈለግ የገነገነ “ዓይነ-ጥላ” ያለበት ድርጅት መሆኑን ስለምገነዘብ የኔን አቋሞች እዚህ ላይ አካቶ ማቅረቡ ጠቃሚ መስሎ ስላልታየኝ አላካተትኳቸውም። ህወሓት ከግራ-ፖለቲካ ጋር ተጣብቶ በማደጉ ምክንያት ካዳበራቸው ፀረ-ዴሞክራሲ የሆኑ ባህሪዎች መላቀቅ ካልቻለ በስተቀር የራሱንም ሆነ የትግራይን ህዝብ ችግሮች ሊፈታ፣ ሌሎች አሱን በሚመለከት ያላቸውን አሉታዊ አመለካከትም በአንፃራዊነት ቀይሮ በአገር ደረጃ አዎንታዊ ሚና ለመጫወት አይበቃም።

የትግራይ ህዝብ ባአለፉት ሁለት የጦርነት ዓመታት የደረሰበት ግፍና በደል በየትኛውም ውድ ዋጋ ሊካስ የሚችል አይደለም። ቢያንስ ግን ከዚህ ሁሉ መስዋዕትነት በኋላ የትግራይ ህዝብ ከህወሓት ብቸኛ ቁጥጥር ነፃ በመውጣት ተጨባጭ የዴሞክራሲ ስርዓት ጅማሮ ውስጥ ካልገባና በመድሃኒት እጦትና በረሃብ ከመሞት መዳን ካልቻለ የሚሊዮን ልጆቹ የህይወት መስዋዕትነት “ደመ-ከልብ” ሆኖ ቀርቷል ማለት ነው። በተለይም በዚህ ወቅት የህወሓት ካድሬዎች የእርዳታ እህል ዘረፋ፣ የአካል ጉዳተኞችንና የተቃዋሚዎችን ሠላማዊ ሰልፍ ከለከሉ፣ በስልጣን ጥያቄም እየተሻኮቱ ነው ወዘተ… መባልን ስንሰማ የትግራይ ህዝብ ችግሩ ሊፈታለት የተቃረበ መሆኑ ሳይሆን የበለጠ አደጋ ከፊቱ እየጠበቀው እንደሆነ እንገነዘባለን። ምናልባትም ትግራይ ወደ ‘ድህረ አፄ ዮሃንስ’ ሁኔታ ልትገባ ይሆን? የሚል ስጋትም ይፈጥራል።

በአጠቃላይ “ኃይል ነው’ የተባለው የእስካሁኑ የፖለቲካ መስመር ዴሞክራሲንና ዘላቂ ሠላምን ካላመጣና ህዝቡን በረሃብ ከመሞት ካልታደገ ተሸቀንጥሮ ሊጣል የሚገባው እንጂ የኩራት መገለጫ የሆነ መፈከር ሆኖ ሊቀጥል አይገባም። ህወሓት ከዚህ አብሮት ከኖረና ለውድቀቱ ዋና ምክንያት ከሆነው መዋቅራዊ ድክመቱ በመላቀቅ ወደ አዲስና እውነተኛ የለውጥ ምዕራፍ መሸጋገር ከፈለገ “መስመር እዩ ኃይልና!” በፍጥነት ወደ “ዴሞክራሲ እዩ ኃይልና!” መቀየር አለበት።

**ልደቱ አያሌው**

**ጥር 17 ቀን 2016 ዓ. ም**